thl

የሴቶች ግርዛት

thl.fi/fgm



# የሴቶች ግርዛት

**የሴቶች ግርዛት (የሴቶች ብልት ግርዛት፣ FGM) የሴተችን የውጨኛውን ብልት ያለ ህክምና ምክንያት መቁረጥ ወይ ጉዳት ማድረስ ማለት ነው።**

የሴቶች ግርዛት ከባህል ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህም ኣብዛኛውን ግዜ የሚካሄደው ህፃናትን በመጠበቅ ስም ነው።ቤተሰቦች በማህበራዊና ስነምግባራዊ ምክንያቶች ይህን እንዲቀጥሉ ተፅዕኖ ሊደርስባቸው ይችላል፡ ፡ ሴቶች ከራሳቸው ባህልና ቤተሰብ ጋር ለማገናኘት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። የሴቶች ግርዛት በፊንላንድ ውስጥ ሰብአዊ መብት ጥሰትና ወንጀል ነው። ጥቃት የሚደርስባት ሴት የፊንላንድ ቋሚ ነዋሪ ከሆነች፤ ምንም እንኳን ግርዛቱ ከፊንላንድ ውጪ ቢካሄድም ወንጀል ነው። የተለያዩ የሴቶች ግርዛት ዓይነቶች ኣሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፣ ብልት ውስጥ ትንሽ ቀዳዳ ወይም መቆረጥ እና በጣም ሥር ነቀል በሆኑ ቅርጾች፣ ውጫዊ የብልት ክፍል ከሞላ ጎደል ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ሊሆን ይችላል። የሴቶች ግርዛት ምንም ዓይነት የጤና

amhara

thl.fi

ጥቅሞች የሉትም። አብዛኛው ግዜ ደም መፍሰስ፣ ኢንፌክሽን፣ ህመምና የስነ አእምሮ ጤናዎች ችግር የመሳሰሉ የጤና ችግሮች ያስከትላል።

## ነገር ግን፣ በሴቶች ግርዛት ለሚከሰቱ ችግሮች ድጋፎች ቀርበዋል።

### የመክፈት ቀዶ ጥገና፤

- በመክፈት ቀዶ ጥገና፣ የተዘጋው ላብያ እንዲከፈት ይደረጋል። ይህም ከወር አበባ፣ መሽናት፣ ወሲባዊ ግንኙነትና ልጆች መውለድ ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሆን ይችላል።
- አብዛኛው ግዜ ይህ ቀዶ ጥገና በግማሽ ማደንዘዣ በፍጥነት ይሰራል። በተጨማሪም በእርግዝና ወቅት ሊካሄድ ይችላል።

### መልሶ መጠገን ቀዶ ጥገና፤

- መልሶ መጠገን ቀዶ ጥገና የተለመደውን የሴቶች ብልት ቅርፅና ስራ መልሶ ለመገንባት ያቀደ ነው።
- ይህ ቀዶ ጥገና በማደንዘዣ የሚካሄድ ነው።
- ፊንላንድ ውስጥ የዳግመ መጠገን ቀዶ ጥገና በመንግስት የጤና እንክብካቤ ስር ይቀርባል። የዳግመ መጠገን ቀዶ ጥገና በ HUS ፕላስቲክ ቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ይካሄዳል።

## FGM ባህል የጤና ችግር ያስከትላል እንዲሁም ወንጀል ነው። በጋራ ይህን ጎጂ ባህል ሰንሰለት እንስበር!

### ድጋፍ ያገኛሉ

የሴቶች ብልት ግርዛት አደጋ ስጋት ላይ ከሆኑ፣ ወደ ፖሊስ በ112 በመደወል ያነጋግሩ ወይም ስለሁኔታው ለማህበራዊ ደህንነት ወይም የጤና እንክብካቤ ባለሙያ፣ አስተማሪ ወይም ሌላ ባለሙያ ያሳውቁ።

**ነላሊንጃ የቤት ውስጥ ጥቃት መከላከል**
nollalinja.fi/en or call 080 005 005

**መጠለያዎች**
nollalinja.fi/en/shelters-for-victims-of-domestic-violence

**African Care:** africancare.fi

**The Finnish League for Human Rights:** ihmisoikeusliitto.fi/english

## ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት

thl.fi/fgm

THL Work against violence
thl.fi/vakivalta